
# ያካባቢ ጉዳይ በኢትዮጵያ




አዘጋጅ

[illegible]

ከፍያለው አባተ

## <u>*መጽሐፍ ግምገማ*</u>

***"ያካባቢ ጉዳይ በኢትዮጵያ፣ ልብ ወለዳዊ የንባብ መጽሐፍ"***

***<u>ደራሲ</u>፣ ዶ/ር ከፍያለው አባተ***

***<u>ገምጋሚ</u>፣ ዶ/ር ጌታቸው መልኬ***

***"ያካባቢ ጉዳይ በኢትዮጵያ" ስላካባቢ ሁኔታ የሚያስተምር በምርምር ላይ የተመሠረተ ጥናታዊ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በልብወለድ መልክ እየተተረከ አካባቢ ሁለገብና የብዙ ነገሮች ትስስር መሆኑን ይገልጻል። ልብወለዳዊ ትረካው ሳይንሳዊ ትንተናውን በሚያጠናክር መልኩ በጥንቃቄ በተመረጡ የቃላት ስብጥር የአንባቢያንን ስሜት በሚስቡና በሚያዝናኑ ማራኪ በሆኑ ዓረፍተ ነገሮች፣ ግጥሞችና ዘይቤዎች በአባ እንዳለው መላኩና በሌሎች ግለሰቦች/ ተሳታፊዎች ተተርከዋል። ምናልባት አንዳንዶቹ ቃላቶች የዘመኑ የከተሜ ወጣት ሊረዳቸው እንደማይችል እገምታለሁ።***

***የመጽሐፉ አጀማመርና ትኩረት በሰሜኑ ክፍል ሀገራችን ላይ ቢሆንም ትንተናው መላ ኢትዮጵያን የሚሸፍንና ከዚያም አልፎ ዓለም ዓቀፋዊ ይዘት እንዳለው መረዳት ይቻላል።***

## <u>*የመጽሐፉ ይዘት*</u>

***መጽሐፉ በ23 ምዕራፎች* ተከፍሎ በ 453 ገጾች የተጠቃለሉ በርካታ ርዕሶችን አካቷል። ርዕሶቹም ተደጋጋፊና ተዛማጅነት አላቸው። አልፎ አልፎ በአንዱ ርዕስ ስር የተገለጹት ሁኔታዎች በሌሎች ርዕሶችም ስር በተለየ አቀራረብ ተደግመዋል። ርዕሶቹ በርካታና በያንዳንዱ ርዕስም ስር ሰፊ ቁምነገር ያላቸው ሀሳቦች ተተንትነዋል። የመጽሃፉ መሠረታዊ ሃሳቦች ጠቅለል ባለመልኩ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት ተገምግመዋል።***

***መጽሐፉ የኢትዮጵያን መልክዓ ምድር በመግለጽ ይጀምራል። በተለይም በሰሜኑ ክፍል ሀገራችን ላይ ያተኩራል።***

***<u>መልክዓ ምድር</u>፤- የኢትዮጵያ መልክዓ ምድር በደጋ፣ በወይና ደጋና በቆላ የተከፈለ ሆኖ ብዙ ተራሮች፣ሸንተረሮች፣ ወንዞች፣ደኖች፣ የተለያዩ የአየር ጠባዮችና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ያሉት መሆኑን መጽሐፉ ያመለክታል። የመልክዓ ምድሩ አቀማመጥ የሕብረተሰቡን አሰፋፈር ያኗኗሩን ዘዴ፣ባህሉንና ልማዱን እንደወሰነው ጽሁፉ ያስረዳል። ይህ የሕዝብ አሰፋፈር ልማድና ባህል ለልማት ስራ አስቸጋሪ እንደሆነ ከጽሁፉ ለመረዳት ይቻላል።***

---

**** ደራሲው "ምዕራፍ" የሚለውን ቃል አልተጠቀሙም። በዚህ ግምገማ ለ23 ክፍሎች የተሰጠ ስያሜ ነው። ስህተት ሆኖ ቢገኝ ተወቃሹ ገምጋሚው ነው።***

እንዲሁም ይህ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ ወንዞች የሚፈሱበትንና የሚጓዙበትን አቅጣጫ ይወስናል።ወንዞች ከከፍተኛው ቦታና ከተራራው ስር ተነስተው ወደታች በመፍሰስ በመንገዳቸው ያለውን አፈሩን፣ ኩረቱን፣ድንጋዩን፣ግንዱን፣ ወ.ዘ.ተ. በመውሰድ ከፍተኛውን ክፍል (ደጋውናና ወይና ደጋውን) ያራቁቱታል። ያገር ድንበር አቋርጠው የሚሄዱት ትልልቅ ወንዞችም አፈሩን ከመውሰዳቸውም በላይ ጠላት ሲፈጥሩብን እንደቻሉ በመጽሁፉ ውስጥ ተጠቁሟል። በአጠቃላይ የመልክዓ ምድሩ አቀማመጥ ባካባቢ ላይ አሉታዎ ተጽዕኖ እንዳለው ማወቅ ይቻላል። ለድህነታችንም አንደኛው መንስዔ (ምክንያት) ነው ለማለት ያስደፍራል።

ምዕራፍ አንድ ስለኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ግንዛቤ ካስጨበጠን በኋላ ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ ባብዛኛው በአባ እንዳለው መላኩ ተራኪነትና በሌሎች ብዙ ተዋናኞች (አድባሩ፣ዱባለ፣ጌጤነሽ፣ ወርቄ ወ.ዘ.ተ.) የሚሳተፉበት ልብወለዳዊ ትረካ እስከ ምዕራፍ ሃያ ሶስት ይዘልቃል።

_ባሕል፤-_ የባህላችን ጠቃሚና ጎጅ ልማዶች፣ አመለካከቶችና ተግባሮች የሚያሳዩ ትረካዎች በተለያዩ ርዕሶች ሰፍረው ይገኛሉ። ባካባቢ ላይ ያላቸውንም ተፅዕኖ ይጠቁማሉ። አባ እንዳለው መልካሙ ስለሕብረተሰቡ መተሳሰብ፣ መረዳዳትና መደጋግፍ ሲያስረዱ የሳቸውንና የጓደኛቸውን የአቶ እውንቱ በለጠን ሰርግ በምሳሌነት በማቅረብ ሰፊ ትንተና ያደርጋሉ።

ለሰርጉ ቤተዘመዱም፣ጎረቤቱም በመተባበር ሴቱ እህል በመፍጨት፣ ሊጥ በማቡካት፣እንጀራ በመጋገር፣ወጥ በመስራት ወ.ዘ.ተ. ሲተባበር ወንዱ ደግሞ እንጨት በመቁረጥ፣ ፍልጥ በመፍለጥ፣ ዳስ በመጣል፣ ሸክም በመሸከምና በመሳሰለው ሥራ ይተባበር ነበር እያሉ አባ እንዳለው በዘመናቸው የነበረውን የሕብረተሰብ ትብብር በሰፊው ይተርካሉ።

የድግሱም ሆነ የተቆረጠው እንጨት ብዛት ባካባቢው ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለማሳየት ይመስላል አድባሩ ይህ ባህላዊ ልማድ ቅንብር እንዳልነበረው እህሉ ብቻ ሳይሆን እንጨቱም እንደባከነ አድርጎ እንዳየው አስተያየቱን ይገልጻል። አባ እንዳለውም በዘመኑ የእንጨት ችግር እንዳልነበረና ቅንጅትም እንደማያስፈልገው ካስረዱ በኋላ እጥረትና ችግር በነበረበት የጉልበት ስራ ላይ ግን ቅንብር እንደነበር ያብራራሉ። ይህ ትብብር፣ መረዳዳትና መተሳሰብ የባህላችን መልካም ገጽታ መግለጫ ሲሆን ጎጅ ባህላዊ አመለካከቶችንም ጨምረው ያስረዳሉ።

ባህላዊ አመለካከታችን *"ለሥራም ለሰራተኛም ክብር እንደማይሰጥ"* ለማሳየት አባ እንዳለው እንደሚከተለው ይገልጻሉ። *"ገበሬውን አፈር ገፊ፤ ብረት ሰራተኛውን ጠይብ፣ ቡዳ፤ ነጋዴውን ገጣባ አጣቢና መጫኛ ነካሽ በማለት ቆዳ ማረብ፣ ብረት መቀጥቀጥ፣ ሸክላ መስራት፣ ሸማ መስራት፣ ጌጣጌጥ መስራት (አንጠረኛነት)፣ መሸቀጥ (መቸርቸርና መነገድ) ወ.ዘ.ተ. የሚናቁ 'አጥንተ ሰባራ' የሚያሰኙ ሙያዎች"* የነበሩ መሆናቸውን ያብራራሉ። ይህ ባሕላዊ አመለካከት ለድህነታችን ሌላው ምክንያት መሆኑ ነው።

_ድህነት፤-_ በሕዝብ ብዛት ምክንያት የሚታረሰው መሬት እየጠበበ በመሄዱ ደኑ/ጫካው እየተጨፈጨፈ ለእርሻ እንዲውል ተደርጓል። ይህም ቢሆን መሬቱ አልበቃ እያለ ያለው መሬት እየተሸነሸነ አፈሩ እየተቦረቦረና እየሳሳ በውሃ እየታጠበ ምርታማነቱ እየቀነሰ በመምጣቱ የህዝቡ

ኑሮ ከዘመን ወደ ዘመን እየቆረቆዘ እንጅ እየተሻለ ሲሄድ አልታየም። የቀረው ዛፍም እየተመነጠረ ለቤት መስሪያም ለማገዶም ውሏል። አካባቢውንም በይበልጥ አራቁቷል።

ስለአካባቢው መራቆት ሕዝቡ ግንዛቤ እንዲኖረውና እንክብካቤ እንዲያደርግ የሚያሳስበውና የሚያስተምረው አካልም የለም። ቢኖርም ሕዝቡ በዕለት ተለት ኑሮ ተቀፍድዶ ሰለተያዘ ስለአካባቢ መራቆት እንዲያስብና ጥበቃ/ እንክብካቤ ለማድረግ አልቻለም። በዚህ ሁኔታ ድህነትን ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት ቀላል ሆኖ አልተገኘም። በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ *"ጥቃትን እንጅ ድህነትን አይፈራም"* በሚል ጎጅ አመለካከት ተይዞ ድህነትን መጸየፍና መዋጋት አገርን ከጥቃት ለመከላከል ከሚያስፈልገው በላይ መስዋዕትነት እንደሚጠይቅ አይታየውም።

አባ እንዳለው ድህነትን አስመልክቶ እንደሚከተለው ሰፊ ትረካ ያደርጋሉ።

> *ጥቃትን ብንጠላም በድህነት ታስረን እስከኖረን ድረስ መጠቃታችን አይቀርም። ድህነታችን ሲያስጠቃን ይኖራል። ባሁኑ ዘመን ጠላቶቻችን ድምበር ጥሰው፣ ወታደር አሰልፈው፣ ጦር ሰብቀው አገር መውረር አያስፈልጋቸውም። እግራቸው ካገራቸው ሳይወጣ በዕጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ከኛ ሊወስዱ የሚፈልጉትን መውሰድ ይችላሉ። በተለያየ ዘዴ አጣብቂኝ ውስጥ ያስገቡንና ሳንወድ በግድ ዓይናችን እያየ፣ እየቆጠቆጠን እንድንሰጣቸው የሚያደርጉበት ዘዴ ብዙ ነው። (ገጽ 163-164)*

አባ እንዳለው ጨዋታቸውን ከአድባሩ ጋር በመቀጠል ለድህነታቸን አንዱ ምክንያት የአስተዳደር ብሉሽነትና የፍትህ መጓደል መሆኑን በሰፊው ይተነትናሉ።

> *የኢትዮጵያ ሕዝብ በድህነት መማቀቅ የጀመረው አፈር ከመቦርቦሩ፣ ጫካው ተመንጥሮ ከማለቁ፣ የሚታረስ መሬት ከመጥበቡ በፊት ነው። ለድህነት ከሚዳርጉት ዐበይት ጉዳዮች ውስጥ የአስተዳደር በደልና የፍትህ መጓደል ናቸው (ገጽ 161)።*

*<u>አስተዳደር፤-</u>* የአስተዳደር ጉዳይ ለሕዝብ ብሶትና ችግር መፍትሄ የሚሰጥ ሆኖ አያውቅም። ገበሬው የመሬቱ ብቻ ሳይሆን የንብረቱም የጉልበቱም ባለቤት ሳይሆን ብዙ ዘመናት አልፏል። የፖለቲካው አመራር፣ የኢኮኖሚው አወቃቀር፣የአስተዳደር መዛባት፣ጉቦኝነት፣የፍትህ እጦት ወ.ዘ.ተ. ለእድገት የማያመች፣ ለሥራ የማያነሳሳና የማያበረታታ በመሆኑ ባጠቃላይ ድህነትን ለመዋጋት/ ለማጥፋት አልበጀም። እንዲያውም የሕዝቡን ተስፋ አጨልሞት ይኖራል።

በዘመናችን የተፈጠረው ወይም ጎልቶ የወጣው *"ዓለም አቀፋዊነት"* ሃሳብም ለሕዝቡ የኑሮ መሻሻልና ዕድገት ተስፋ ሰጭ ሊሆን እንደማይችል መጽሐፉ በሰፊው ይተነትናል።

*<u>ዓለም አቀፋዊነት፤-</u>* ይህ ዓለም አቀፋዊነት አስተሳሰብ አነሳሱ በኢኮኖሚ ላይ ማለትም በንግድና በኢንቨስትመንት ውድድር ላይ ያተኮረ ቢሆንም መሠረተ ሃሳቡ የበለጸጉ አገሮች ሌሎች አገሮችን በተለይም "በማደግ ላይ" ያሉ አገሮችን ኢኮኖሚያቸውን ብቻ ሳይሆን ባህላቸውናን ልማዳቸውን፣ አኗኗራቸውን፣ ማህበራዊ ስርዓታቸውን/ትስስራቸውን፣ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውንና አካባቢያቸውን/ የተፈጥሮ ሃብታቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል አዲስ ዓለም አቀፋዊ አመለካከት ነው። ይህ ዓይነት ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ/ሥርዓት ከብልሹና ከኢፍትሃዊ

አስተዳደር ጋር ሲጣመር ድህነትን ለመዋጋት ያለው ዕድል ጠባብ፣ውስብስብና አስቸጋሪ እንደሚሆን ከመጽሐፉ ትንተና ለመረዳት ይቻላል። ይህ የዓለም አቀፋዊነት አመለካከት በዓለም ዙሪያ አገራችን ጨምሮ ባካባቢ ስላለው ተፅዕኖ በ12 ነጥቦች ተከፍሎ በሰፊው ተብራርቷል።

_ኃይማኖትና አካባቢ፤_ የመጽሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ በኃይማኖት ላይ ያተኮረ ሲሆን የተለያዩ ኃይማኖቶችና እምነቶች ስለአካባቢ ያላቸውን አመለካከት በንጽጽር መልክ በዝርዝር ያቀርባል። ሰዎች በእለት ዕለት ተግባሮቻቸው ለምሳሌ ለምግብና መጠጥ የሚሆኑ አቅርቦቶችን ለማግኘት፣ ቤትና መጠለያ ለመስራትና ለሌሎችም ተግባሮች ምን ያህል የሚከተሉት ኃይማኖት ተጽዕኖ እንደሚያሳድርባቸውና ኃይማኖቶችም በተጨባጭ ሁኔታ ላካባቢ ጥበቃ የሚያደርጉት ገምቢና አፍራሽ አስተዋጾዎች በዝርዝር ተገልጸዋል።

## ማጠቃለያ

*"የአካባቢ ጉዳይ በኢትዮጵያ፣ ልብወለዳዊ የንባብ መጽሐፍ"* በ23 ምዕራፎች ተከፍሎ በ453 ገጾች የተጠቃለሉ በርካታ ርዕሶች ዙሪያ ስለአካባቢ ጉዳይ የሚያስተምር ጥናታዊ መጽሐፍ ነው። አካባቢ የብዙ ነገሮች ትስስርና ቁርኝት መሆኑን በሰፊው በልብወለዳዊ ትረካ በመዘርዘር ባካባቢ ጉዳይ ላይ የሚደረገው በደል ለፍጥረታት ሁሉ የሰውን ልጅ ጨምሮ ከፍተኛ መዘዝ እንዳለው መጽሐፉ ያስገነዝባል። መጽሐፉ በመረጃና በጥናት ላይ የተመረኮዘና ትንተናውም ሳይንሳዊ የምርምር ሕግጋትን የተከተለ ነው። በመጽሐፉ ርዕስ ላይ *"ልብወለዳዊ"* የሚል ቅጽል ቢጨመርበትም የሳይንሳዊ ትንተናውን የሚያደበዝዝ ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም ላካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ በድርጅቶችም ሆነ በቡድን እንዲሁም በግለሰብ ደረጃ ሊደረጉ የሚችሉ ብዙ ቁም ነገሮች እንዳሉ ከመጽሐፉ መማር ይቻላል።

በመጨረሻም መጽሐፉ በበሰለና በሰከነ አእምሮ የተጻፈ የምርምር ውጤት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቃለሉት ግጥሞች፣ ጨዋታዎች፣ ትረካዎች አንባቢያንን የሚያዝናኑና የሚያስቁ እንዲሁም ታሪኮቹ ልብ የሚያንጠለጥሉና መጽሐፉን ማንበብ ከጀመሩት ሳይጨርሱት የማያስቀምጡት በመሆኑ ተውኔቶችንና ትያትሮችን ለመስራት ለሚፈልጉ ሁሉ ጠቃሚነት አለው። እንዲሁም መጽሐፉን በትረካ መልክ በሬዲዮ፣ በቴሌቭዥን ወይም በኢንተርኔት ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ ጥሩ አጋጣሚ ነው። መጽሐፉን በማንበብ ስለአካባቢ ጉዳይ ሰፊ ግንዛቤ መጨበጥና የዕወቀት አድማስንም ማስፋት ይቻላል።

መጽሐፉን ለማንበብ የወሰናችሁ ሁሉ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።